በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ መ/ቤት
የፍትሃብሔር ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት

IN THE AMHARA NATIONAL
REGIONAL STATE ATTORNEY GENERAL
CIVIL CASES DIRECTORATE

ቁጥር ፍቢ/1835/መፈ-7

ቀን 28/08/2012 ዓ.ም

ለአብክመ ጤና ጥበቃ ቢሮ

ባህር ዳር፣

ጉዳዩ፡- የግንባታ ውል ማሻሻያን ይመለከታል፣

ከአብክመ ጤና ቢሮ ውል ወስደው የቦሩ ሜዳ አእምሮ ህመ-ማን ማገገሚያ ማዕከልን በመገንባት ላይ የሚገኘው አቢታ ኮንስትራክሽን ድርጅት የግንባታ ስራ ውል ረቂቅ ሲዘጋጅ የክፍያ ሁኔታ በአራት ጊዜ እንዲከፈል የሚገልፅ ሲሆን የውሉ አካል በሆነው የግንባታ ስራዎች መደበኛ የጨረታ ሰነድ ተራ ቁጥር 64.7 ስር ከተመለከተው ጋር የሚቃረን ከመሆኑም በላይ ግዙፍ በሆኑ ፕሮጀክቶች $^{1}/_{4}$ኛ ካልሰሩ በስተቀር ክፍያ መጠየቅ አይችሉም መባሉ በስራ ተቋራጮች ላይ የፋይናንስ እጥረት የሚያስከትል እና ለግንባታ ስራው መጓተት ምክንያት በመሆኑ ማሻሻያ እንዲደረግበት ቅሬታ አቅርበዋል ::

የግንባታ ስራ ክፍያ ተለክቶና በአማካሪ መሃንዲስ ተረጋግጦ በተሰራው ስራ ልክ ብቻ የሚከፈል በመሆኑ ክፍያው 25% እስኪደርስ መጠበቅ ለስራ ተቋራጮች ጫና ከመፍጠሩ በስተቀር ለከሰረው መ/ቤት የሚያስገኘው ጥቀም የለም::

በመሆኑም የውለታ ፎርሙ ወደፊት በሚመረመሩ ውሎች ላይ ተስተካክሎ የሚላክላችሁ መሆኑን እየገለፅን የውሉ አካል የሆነው መደበኛ የጨረታ ሰነድ ከ5% በላይ ለተሰራ ሥራ ክፍያ መጠየቅ እንደሚቻል ስለሚፈቅድ በዚህ አግባብ ክፍያ በመፈፀም የፋይናንስ እንቅስቃሴውን በማቀላጠፍ ግንባታው በታቀደለት ጊዜ እንዲከናወን እንድታደርጉ እናሳስባለን::

ከሠላምታ ጋር

ግዛቸው መስፍን
በአማራ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ
የፍትሐብሔር ጉዳዮች ዳይሬክተር